# “ሲናይ—አበሻን እየዋጠ የሚያስቀር የበረሃ ረግረግ”

“ረጅም የሞትና የእልቂት ጎዳና” ብሎታል ጋዜጠኛው። መከረኞቹ የአፍሪቃ (ባብዛኛው ኢትዮጵያዊያንና ኤርትራዊያን ናቸው) ስደተኞች በብረት ሰንሰለት ተቆላልፈው ከዛፍ ጋር ይታሰራሉ። ሽንታቸውን የሚያጠራቅሙበት የላስቲክ ከረጢት ይታደላቸዋል--ሲጠማቸው እንዲጠጡት። በርብርብ (gang raped) ይተኗቸዋል። *(አንድ ጸሃፊ [ቤልጅግ አሊ የሚባሉ በጻፉት ውስጥ ይመስለኛል] ያኔ በደርግ ጊዜ ስለነበረው ግርፋት “... ካልሲውን እንደኳስ ጠቅልለው አፋችን ውስጥ ይከቱት ነበር..” ብሎ ላንዱ በአረብ በረሃዎች አቆራርጦ ስካንዲኒቪያን የደረሰ ወጣት ቢነግረው “...አይ ጋሽ፣ እናንተ ካልሲ ነው የጎረሳችሁት እኛ ግን....” ብሎ ስቅስቅ ብሎ ያለቀሰውን ውጣት አስታወሰኝ።*

ስደተኞቹ እስረኞች በኤሌክትሪክ ይቀረቻሉ። ለማምለጥ ሲሞክሩ በጌቶቻቸው (በራሻይዳ በድዊን ጎሳዎች) ወይም በግብጽ ፖሊሶች ይገደላሉ። ይህ በሲናይ የግብጽ በርሃ ውስጥ በኢትዮጵያዊያንና ኤርትራዊያን ላይ እየደረሰ ያለው ‘ሳቤጅ’ እና የሚረብሽ ዜና ባለፉት ጥቂት አመታት ውስጥ ጥሩ የዜና ቁርስ ሆኗል።

ኢትዮ-ኤርትራዊያንን ያካተተው ይህ አይነቱ ዜና የጀመረው፣ ምናልባትም ከ2000 አ.ምህረቱ የሁለቱ አገሮች ጦርነት ፍጻሜ በኋላ ነው። ያጦርነት ነው ያን ሁሉ ስደተኞች የፈጠረው።

በ2005 ግብጽ ስደተኞቹን ማሳደድ ጀመረች። ፖሊሶቹ የሚሰፍሩበትን ካምፕ አካባቢ ለማጽዳት ብቻ በአንድ ወቅት ከ10 እስከ 60 የሚሆኑ ስደተኞችን ገድለዋል። ከ2007 ጀምሮ እስራኤል ውስጥ የኤርትራዊያን ስደተኞች ቁጥር ከ10ሺህ በላይ ሲሆን፣ ከፍተኛውን ቁጥር ይዘዋል። አንዱ ስደተኛ “...በሰውነቱ ላይ የፈላ ውሃ እንዳፈሰሱበት ...” ተናግሯል። በአንድ ሌላ ወቅትም 139 ስደተኞች የት እንደደረሱ አይታወቅም።

ከጁላይ 2007 እስከ ኦክቶበር 2008 ድረስ በመገናኛ ብዙሃን የተነገረ 33 ስደተኞች ከግብጽ ወደ እስራኤል ሲሻገሩ ተገድለዋል።

በማርች 2010 ከ60 በላይ ተገድለዋል። ይህን የግድያ ፖሊሲ እንዲያስፈጽሙ የተሾሙት የሰሜን ሲናይ ገዢ የሆኑት ጀኔራል ሙሃመድ ሾውሻ ናቸው። ጀኔራሉ “መግደላችን ስህተት የለበትም። መግደል አስፈላጊ ነው። ሰርጎ ገቦች ጋር መደራደር አያስፈልግም፣ መተኮስና መግደል ነው” ብሏል። ግብጻዊያኑ፣ ህጻናትንና ሴቶችን ሳይቀር ተኩሰው እንደሚገድሉና “... እናንተ የአረብና እስላም ጠላቶች ናችሁ” እንደሚሏቸውም አንዱ ከሞት የተረፈ ስደተኛ ተናግሯል።

ዮሴፍ እና አሊ የተባሉ ኢትዮጵያዊያን በሲናይ በረሃ የበድዊን ጎሳዎች ስለሚያደርሱት በደልና እንዴት መያዣ (Ransom) እንደሚያደርጓቸው... የመያዣው ገንዘብ እንዴት ከእስራኤል ወጥቶ ባድዊኖቹ እጅ እንደሚገባም አስረድተዋል።

ዘመናዊ ባርነት ዛሬም አለ። አንዷን ኤርትራዊ እጅ እግሯን አስረው ... እስራኤል ያሉ ዘመዶቹዋ $2800 ካልከፈሉ ኩላሊቷን አውጥተው እንደሚሸጡት... ሌላዋ ኤርትራዊ ደግሞ

በሲናይ በረሃ 8 ወንዶች በርበርብ እንደደፈሯት ተናግራለች። በዚያው ወር የ10 ስደተኞች አስከሬን ማንነታቸው እንዳይታወቅ ተደርጎ ተቆራርጠው ተጥለው ተገኝተዋል። …

በቅርቡ ኦገስት 14/2010 በበድዊን የማገቻ ሰፈር 300 ስደተኞች ታግተው ነበር። አንዱ እስረኛ እንደምንም ከጠባቂው መሳሪያ ሰርቆ (እኔ ማርኮ ነው የምለው) ብዙዎቹን አስለቀቀ። በትኩሱ ምልልስም ስድስት ኤርትራዊያን ተገድለዋል። የግብጽ ፖሊሶች ደርሰው እያመለጡ የነበሩ ሁለት ኤርትራዊያንን ገድለው 17ቱን አስረዋል። … ግብጻዊያኑ ፖሊሶች የስደተኞቹን መገደል ወይም መጥፋት የፈለጉት ይመስላል። ….።

**ይህ ከዚህ በላይ የሰፈረው የራሴ ትርጉም ነው።**
**ምንጭ፡-** http://www.jpost.com/Opinion/Columnists/Article.aspx?id=185084

&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&

ግብጽ፣ ኤርትራን የመገንጠል አላማ ይዞ የተነሳውን የመጀመሪያውን፣ የኡስማን ሳልህ ሳቤን ድርጅት ያበረታታችና የመጀመሪያውን ቢሮ በካይሮ እንዲከፍቱ የፈቀደች ብቻ ሳትሆን በሎጂስቲክስና መሳሪያ ሁሉ ሻእቢያን እያገዘች እዚህ ያደረሰች አገር ነች። ግብጽ ዛሬ "አንተ ኤርትራዊ ነህና … አንተ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ነህና…" ብሎ መለያም መመዘኛም የላት። የግብጽ አላማና ፍላጎት አንድና አንድ ነበር—አባይን ከምንጩ፣ ቀይባህርን ደግሞ ካናቱ ጀምሮ መቆጣጠር። ለዚህ ደግሞ ደካማና የተቆራረጠች ኢትዮጵያን መሰራት።

ዛሬ የወያኔው መለስና የሻእቢያው ኢሳያስ፣ የግብጽን ጆሮ ለማግኘት እሽቅድምድም ላይ ያሉ ይመስላሉ። *(የመለስ ደጋፊዎች የሰሞኑ ያሜሪካ አገር የ'ኢትዮጵያ የናይል ወንዝን የመጠቀም መብት አላት' ሰልፍ እንዲያው 'ብላኔ' ነው—ሽፋን። መለስ የናይልን አጠቃቀም በተመለከተ ሙሉ ይሁንታውን ለግብጾች የሰጠበትንና ከሆስኒ ሙባረክ ጋር የተፈራረመውን ውል አስመልክቶ በርካታ ጸሃፍት የጻፏቸውን ደግሜ እዚህ አላነሳም)።*

&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&

"ከነዚህ ሰዎች ጋር አንድ ላይ ብንቆም ይህን ገዢ መሬት ይዘን፣ የሚበግረን የውጭ ጠላት ከቶ አይገኝም ነበር። ሁለታችንም ወኔ ለወኔ የምንተዋወቅ ያንዲት ኢትዮጵያ ልጆች ነበርን። ያለመታደል ነው። ለዚህም ነው ይህ ጦርነት እጅግ መራራና አስቃቂ የሚሆነው" ኤርትራዊው ኮሎኔል ታሪኩ ወልዳይ (ኦሮማይ፣ ገጽ 293።)

&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&&

ኢሳያስና መለስ ዛሬም የሆስኒ ሙባረክን ልብ ለማግኘት እየተሟሟቱ አሉ። በስደት የሲናይ የበረሃ ረግረግ እየዋጠ ላስቀራቸው ኤርትራዊያንና ኢትዮጵያዊያን ወንድሞቼና ህቶቼ ብቻ ሳይሆን፣ በጅላጅሉና ጨካኙ ደርግና አሁንም በፖለቲካ ንግድ የከበሩትና፣ መሰሪና ጨካኝ በሆኑት በወያኔና ሻእቢያ መሪዎች ያስተሳሰብ ድህነት ምክንያት ከሁሉም ወገን ላለቁት ወገኖቼ ልቤ ሁሌም ሲደማ ይኖራል።

Gelanew-kirar@hotmail.com